የብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

የባለ አክሲዮኖች አንደኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባ

ታህሳስ 2፣ 2003 ዓ.ም

BIB

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.

BERHAN INTERNATIONAL BANK S

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

BERHAN INTERNATIONAL BANK S.C.

የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት

እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 3 ቀን 2009 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2010

ታኅሣሥ 2 ቀን 2003 ዓ.ም.

የብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት

1. አጠቃላይ

የብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 3 ቀን 2009 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2010 ያለውን የባንኩን የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ዘገባ የባንኩ ባለቤት ለሆናችሁት ባለአክሲዮኖች በዚህ የመጀመሪያ በሆነው ጉባኤ ሲያቀርብ በታላቅ ደስታ ነው፡፡

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ በተፈቀደ 300 ሚሊዮን ብር፣ በተመዘገበ 137 ሚሊዮን ብር እና በተከፈለ 95.7 ሚሊዮን ብር ካፒታል እንዲሁም ከ 6,200 በላይ ባለአክሲዮኖች እ.ኤ.አ ሰኔ 27 ቀን 2009 ሁሉአቀፍ የንግድ ባንክ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን ፈቃድ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመውሰድ መቋቋሙ ይታወሳል ፡፡

ባንኩ በበጀት ዓመቱ ባንኩን በማደራጀትና ሥራ በማስጀመር ለቀጣይ ስኬታማ ጉዞ መሠረት የሚሆኑ በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል ፡፡

ባንኩ ሥራ የጀመረበት ዓመት ዓለም ካጋጠመው የኤኮኖሚ ቀውስ ተጽእኖ የተነሣ በአገሪቱ ኤኮኖሚ ላይ የዋጋ ግሽበትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግሮች የተደቀኑበት ጊዜ እንደነበረ የታወቀ ነው፡፡

የዋጋ ግሽበቱ በራሱ እና ኤኮኖሚውን ለማረጋጋት በመንግሥት የወጡ ገንዘብ ነክ የኤኮኖሚ መመሪያዎች በተለይም የባንኮች የማበደር ጣሪያ መቀመጥ ገና ጀማሪ ለሆነው ባንካችን በአገልግሎት ማስፋፋት እና ትርፋማነት ላይ ቀጥተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፏል፡፡

የባንክ ባለሙያዎችን በማፈላለግ እና ባንኩን በሰው ኃይል ማደራጀቱ ፣ ለቅርንጫፍ የሚሆኑ ጽሕፈት ቤቶች በተመረጡ ከተሞችና ቦታዎች በማፈላለግ የመከራየትና አስፈለጊውን የቢሮ መሣሪያዎችን የማዘጋጀት እና ቴክኖሎጂ የማስገባት ሥራዎችን ማከናወን በባንኩ ኢንዱስትሪ እያደገ ከመጣው ውድድር ፣ የቤት ኪራይ ዋጋ መናር፣ የቢሮ ዕቃዎችና መሳሪያዎች እጥረት እንዲሁም የብሮድ ባንድ መስመር በቀላሉ አለመገኘት አንጻር አስቸጋሪና ብዙ ጥረት እና ትጋት የጠየቀ ነበር ፡፡

ሆኖም ግን ባንኩ እነዚህን ፈታኝ የነበሩትን የምስረታ፣ ባንኩን የማደራጀት እና ሥራ የማስጀመር ምዕራፍ አልፎ የተሻለ እና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ወደ ተዘጋጀበት ቀጣይ ምዕራፍ የተሸጋገረበት ጊዜ ላይ መድረሱን ስገልጽ ደስታ ይሰማኛል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ባንኩ ሙሉ በሙሉ ከኪሣራ ወጥቶ ትርፍ እያስመዘገበ የሚገኝ ሲሆን በቅርቡ ተጨማሪ ቅርንጫፎችን በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች በመክፈት የአገልግሎት አድማሱን ከፍ ያደርጋል፡፡

የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ከዚህ በመቀጠል በበጀት ፤ዓመቱ ባንኩ ያከናወናቸውን ዋና ዋና ሥራዎች በዝርዝር እንደሚከተለው አቀርባለሁ፤

2. የባንኩ ዋና ዋና አገልግሎቶች ክንውን

2.1. የተቀማጭ ሂሳብ

ባንኩ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 ብር 238 ሚሊዮን ጠቅላላ ተቀማጭ ገንዘብ የሰበሰበ ሲሆን፣ ይህም በተቀማጭ ሂሳብ ዓይነት ሲተነተን፤ የተንቀሣቃሽ ሂሳብ ብር 72.8 ሚሊዮን፣ የቁጠባ ሂሳብ ብር 72.9 ሚሊዮን እንዲሁም የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ብር 92.3 ሚሊዮን ነው፡፡

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 የባንኩ አጠቃላይ የተቀማጭ ሂሣብ ደንበኞች ብዛት 4,516 በላይ ደርሷል ፡፡

2.2. ብድር

የባንኩ አጠቀላይ የብድር ክምችት እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2010 ብር 153.2 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ይኸውም ብሔራዊ ባንክ ለባንኩ ያሰቀመጠው የማበደር ጣሪያ ብር 154 ሚሊዮን ሙሉ በሙሉ ተጠቅሟል ፡፡

በበጀት ዓመቱ የባንኩ ተበዳሪዎች ቁጥር 126 የደረሰ ሲሆን የብድሩ ስርጭት በኢኮኖሚ ዘርፍ ሲታይ እንደሚከተለው ነው ፡፡

ተ.ቀ.	ኢኮኖሚ ዘርፍ	የብድር ክምችት መጠን (በሚሊዮን ብር)
1.	ወጪ እና ገቢ ንግድ	55.8
2.	ሆቴልና ቱሪዝም	28.9
3.	አገር ውስጥ ንግድ	27.3
5.	ሕንጻና ግንባታ	15.4
6.	ትራንስፖርትና መገናኛ	14.8
7.	ኢንዱስትሪ	9.2
8.	እርሻ	1.5
9.	ሌሎች	0.3
	ጠቅላላ	153.2

2.3. የአለም አቀፍ የባንክ አገልግሎቶች

ባንኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ የዓለም አቀፍ ስዊፍት አባል በመሆንና ታዋቂ ከሆኑ የጀርመን፣ የአሜሪካ ፣የጣሊያን እና የፈረንሳይ ባንኮች ጋር የኮርስፖንደንት ባንኪንግ ግንኙነት በመፍጠር የተሟላ የአለም አቀፍ የባንክ አገልግሎቶችን ሲሰጥ ቆይቷል ፡፡

በዚህም ረገድ እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2010 ድረስ ባንኩ 4.0 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከተለያዩ ምንጮች ማሰባሰብ ችሏል፡፡ ይህም በቅደም ተከተል ወደ አገር ውስጥ ከተላከ ሃዋላ ፣ ከወጪ ንግድ የተገኘ ፣ ከብሔራዊ ባንክ የተገዛ እና ከውጭ ምንዛሪ ግዢ የተገኘ ነው ፡፡

3. የፋይናንስ ክንውን

በኦዲተሮች በተረጋገጠውና ከዚህ ሪፖርት ጋር አባሪ በተደረገው መሠረት የባንኩ የፋይናንስ ክንውን እንደሚከተለው ነው ፡፡

3.1. ገቢ

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 የባንኩ አጠቃላይ ገቢ ብር 8.3 ሚሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5.8 ሚሊዮን ከወለድ ብር 1.7 ሚሊዮን ከዓለም አቀፍ የባንክ አገልግሎት የተገኘ፣ እንዲሁም ብር 701,992 ከሃገር ውስጥ የባንክ አገልግሎቶች በኮሚሽን እና በአገልግሎት ክፍያ የተገኘ ነው፡፡

3.2. ወጪ

በተመሳሳይ መልኩ የባንኩ አጠቃላይ ወጪ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 ዓ.ም ብር 14.3 ሚሊዮን ደረሷል ፡፡ ከዚህ ውስጥ ጠቅላላ ወጪዎች (General Expenses) ብር 8.5 ሚሊዮን ሲሆኑ፣ ለሠራተኛ ደሞዝና ጥቅም የተከፈለ ብር 4 ሚሊየን እና ለተቀማጭ ሂሳብ የተከፈለ ወለድ ብር 1.8 ሚሊዮን ናቸው ፡፡

ባንኩ ካወጣው ብር 8.5 ሚሊዮን ጠቅላላ ወጪ (General Expenses) ውስጥ ብር 2.3 ሚሊዮን የእርጂና ቅናሽና ባንኩን የማቋቋሚያ (Depreciation and Amortization) ወጪ ሲሆን ብር 1.5 ሚሊዮን ለሚበላሹ ብድሮች መጠባበቂያ (Provision for Loans) የተያዘ ነው ::

3.3. ትርፍ እና ኪሳራ

ባንኩ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 ብር 5.9 ሚሊዮን ኪሣራ አስመዝግቧል :: ይህም ኪሣራ ባንኩ የዘመናዊ የባንክ ቴክኖሎጂ ባለቤት እንዲሆን ከተደረገው ወጪና በአጭር ጊዜ ውስጥ የአገልግሎቱን አድማስ በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች ከማስፋፋቱ አኳያ የሚጠበቅ ከመሆኑ ባሻገር ባንኩ ወደፊት ውጤታማና ትልቅ ባንክ ለማድረግ መሠረት የጣለ ነው::

ለዚህም ማሳያው በአሁኑ ጊዜ የባንኩ የኪሣራ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተቀይሮ ትርፍ በማስመዝገብ ላይ መገኘቱ ነው::

3.4. አጠቃላይ ሀብት

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 የባንኩ አጠቃላይ ሀብት ብር 379.5 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ይህም በዝርዝር ሲታይ ብር 8.3 ሚሊዮን ቋሚ ንብረት ፣ ብር 151.7 ሚሊዮን ብድር መጠባበቂያ ተቀንሶ ፣ ብር 196.9 ሚሊዮን በባንኩና በሌሎች የተለያዩ ባንኮች ያለ ፣ እንዲሁም ብር 22.6 ሚሊዮን ሌሎች ንብረቶች ናቸው ::

3.4. ካፒታል

ባንኩ በ95.7 ሚሊዮን የተከፈለ ካፒታል ሥራ የጀመረ ሲሆን እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 ካፒታሉ 108.3 ሚሊዮን ድርሷል፡፡

የባንካችን የካፒታል አቅም ከሌሎች ባንኮች ጋር ሲወዳደር አነስተኛ በመሆኑ የካፒታል አቅምን የማሳደጉ ሥራ ጠንክሮ መቀጠል እንዳለበት ያመላክታል፡፡

4. የቅርንጫፍ ስርጭት

ባንኩ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 የቅርንጫፍ ስርጭቱን ስምንት አድርሷል ፡፡ ከነዚህም ውስጥ አምስቱ በአዲስ አበባ ከተማ፣ ቦሌ፣ ሃያሁለት ማዞሪያ፣ አመዴ ገበያ ፣ ገነት ሆቴል አካባቢ እና ቃሊቲ የሚገኙ ሲሆኑ ሶስቱ በክልል ዋና ከተሞች በሃዋሳ፣ አዳማ እና ባህር ዳር ይገኛሉ፡፡

5. የሰው ኃይል ክንውን

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 የባንኩ አጠቃላይ የሠራተኛ ብዛት 138 ደርሷል፡፡ ከዚህም ውስጥ 22 በተለያዩ አመራር ላይ የሚገኙ ፣ 54 የባንክ ባለሙያዎች እንዲሁም 62 ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች ናቸው ፡፡

የሰለጠነ የሰው ኃይል ለቀልጣፋ አገልግሎት ትልቅ ፋይዳ ያለው በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ባንኩ ለሠራተኞቹ ተከታታይ ስልጠናዎች እንዲወስዱ አድርጓል ::

6. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክንውን

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ ማ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመግዛት ከጅምሩ የኮር ባንኪንግ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ በማድረግ ሥራ የጀመረ ባንክ ነው፡፡

ባንኩ ተግባራዊ ያደረገውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ቀልጣፋ እና ለደንበኞች አመቺ የሆነ የባንክ አገልግሎት ለመስጠት ችሏል፡፡

ከዚህም አኳያ ፡

- ደንበኞች እያንዳንዱን የሒሳባቸውን እንቅስቃሴ በኤስ. ኤም. ኤስ. መልዕክት የሚያገኙበትን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ይህንንም አገልግሎት የጀመረ ብቸኛ ባንክ ነው፡፡

- የብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ ቅርንጫፎች በሙሉ በኮምፒውተር መረብ የተገናኙ በመሆናቸው ደንበኞች በየትኛውም የባንኩ ቅርንጫፍ ሂሳባቸውን ማንቀሳቀስ ይችላሉ

- ደንበኞች የቁጠባ ሂሳብ ደብተር የግድ መምጣት ሳያስፈልጋቸው ከሂሳባቸው ወጪ እና ወደ ሂሳባቸው ገቢ ማድረግ ይችላሉ፡፡

- ደንበኞች ፎቶግራፍ ማምጣት ሳያስፈልጋቸው ምስላቸውን በዌብ ካሜራ አማካኝነት በመውሰድ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ

በተጨማሪም ባንኩ በሥራ ላይ ያዋለው ቴክኖሎጂ ሌሎች ዘመናዊ የባንክ አገልግሎቶችን ማለትም በመክፈያ ካርድ (payment card) የሚሰጡ የኤ. ቲ. ኤም እና የፖይንት ኦፍ ሴል ፣ የኢንተርኔት፣ የኤስ. ኤም. ኤስ. እና የቴሌፎን የባንክ አገልግሎቶችን በቀጣይ ለመስጠት የሚያስችል ነው ፡፡

7. የባንኩ የወደፊት የትኩረት አቅጣጫ

ባንኩ በቀጣይ የሥራ ዘመን ውጤታማና ተወዳዳሪ የሚያደርገውን እቅድ እና ስልት ነድፎ በሚከተሉት ዋና ዋና የባንኩ የአገልግሎቶች ዘርፎች ዙሪያ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

1ኛ. ተጨማሪ ቅርንጫፎችን በተጠኑ አካባቢዎች መክፈት ፣

2ኛ. ተወዳዳሪ የወለድ መጣኔ በመስጠት የባንኩን የተቀማጭ ገንዘብ ማሳደግ ፣

3ኛ. ባንኩ የተቀመጠለትን የብድር ጣሪያ በአፋጣኝ በመጠቀም ከወለድ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ፣

4ኛ. የዋስትና አገልግሎትን በማስፋፋት የኮሚሽን ገቢን ማሳደግ ፣

5ኛ. ከትልልቅ ኤክስፖርተሮች እና የአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመስራት ፣ የውጭ ምንዛሪ ክምችትን ማሳደግ ፣

6ኛ. በአገልግሎት ክፍያ ላይ የተመሠረቱ አዳዲስ የባንክ አገልግሎቶችን በመጀመር ገቢን ማሳደግ ፣ይቻል ዘንድ የባንኩን ቴክኖሎጂ አቅም ሙሉ በሙሉ

መጠቀም፣

7ኛ. በብርሃን ኢንሹራንስ ኢንቨስትመንት እና በሌሎች አዋጪ የኢንቨስትመንት መስኮች መሳተፍ፣ እንዲሁም

8ኛ. የካፒታል አቅምን ማጎልበት ናቸው ፡፡

ከዚህም አኳያ የተከበራችሁ የባንኩ ባለቤት የሆናችሁ ባለአክሲዮኖች እያንዳንዳችሁ ፤

- በባንካችሁ ሂሳብ በመክፈት ገንዘብ እንድታስቀምጡና ሌሎች ደንበኞችን እንድትጋብዙ ፣
- ኤክስፖርተሮች እንዲሁም አለም ዓቀፍ ድርጅቶች የባንኩን አገልግሎት እንድትጠቀሙ ፣
- የባንኩን የዋስትና አገልግሎት እንድትጠቀሙ
- ከውጭ ወደ አገር ቤት ገንዘብ የሚላክላችሁ በባንኩ በኩል እንዲመጣ እንድታደርጉ ፣
- ተጨማሪ አክሲዮን እንድተገዙና

በጋራ ባንኩን ውጤታማ እንድታደርጉ የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክብሮት ጥሪውን ያቀርባል፡፡

8. ምስጋና

ባንኩ እዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉት አካላት፣

- ከሁሉ በፊት ባንኩ በእግሩ እንዲቆም ከምስረታ ጀምሮ ድጋፋቸው ያልተለየንን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ፣ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽሕፈት ቤት እንዲሁም ባንኩ ከጅምሩ ተግባራዊ ያደረገውን አዲስ ቴክኖሎጂ እውን እንዲሆን ለረዱን የኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን ኮርፖሬሽን ፣

- ለባንኩ ህልውና መሠረት በመሆን ባንኩ ከረቂቅ ኃሳብ ወደ እውነታ እንዲመጣ ምክንያት ለሆናችሁት ባለአክሲዮኖች ፣
- በባንኩ አመኔታ በማሳደር የባንኩን አገልግሎት በመጠቀም ባንኩን ውጤታማ ላደረጉ የባንኩ ደንበኞች በተለይም ኤክስፖርተሮች ፣ እንዲሁም
- ባንኩን ዕለት ከዕለት በትጋት በመሥራት እዚህ ያደረሱትን የባንክ አመራር እና ሠራተኞች

ለሁሉም ከፍተኛ የሆነ ልባዊ ምስጋናን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ በራሴን በዳይሬክተሮች ቦርድ ስም አመሰግናሁ፡፡

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ !

BIRHAN INTERNATIONAL BANK S.C
BALANCE SHEET
AS AT JUNE 30, 2010

Assets employed	Notes	Birr	Birr	30/09/09 Birr
Fixed Assets	3		8,339,452	3,874,551
Deferred expenditure	4		5,599,860	5,621,646
Deferred tax asset			83,596	-
CURRENT ASSETS				
Stocks	5	3,505,782		534,028
Loans & advances	6	151,660,741		-
Other assets	7	13,463,088		1,246,920
Cash on hand and at bank	8	196,867,531		87,819,167
		365,497,142		89,600,115
CURRENT LIABILITIES				
Creditors	10	36,247,873		451,174
Deposits: demand	9 (a)	72,764,985		-
Saving	9 (b)	72,942,787		-
Fixed time	9 ©	92,302,995		-
		274,258,640		451,174
Net current assets			91,238,502	89,148,941
			105,261,410	98,645,138
Refund to shareholders			(2,902,752)	(2,850,038)
Net assets			**102,358,658**	**95,795,100**
FINANCED BY				
Paid up capital	13		108,324,930	95,795,100
Accumulated loss			(5,966,272)	-
			102,358,658	**95,795,100**

Board Chairman

President

BIRHAN INTERNATIONAL BANK S.C
PROFIT AND LOSS ACCOUNT
FOR THE PERIOD ENDED 30JUNE,2010

	Note	Birr	Birr
NTEREST INCOME	14	5,854,990	
NTEREST EXPENSES		(1,837,228)	
ET OPERATION INCOME		4,017,762	
ON-INTEREST INCOME	15	2,420,555	
			6,438,317
XPENSES			
Salary and benefit	16	4,025,499	
General and administrative expenses	17	6,680,173	
Directors fee		203,213	
Provision for loans and advances		1,533,300	
Audit fee		46,000	
			(12,488,185)
Loss for the year			(6,049,868)
Deferred tax asset	11		83,596
Loss carried forward			**(5,966,272)**

Board Chairman

President

BIRHAN INTERNATIONAL BANK S.C

STATEMENT OF CASH FLOW

FOR THE PERIOD ENDED 30JUNE,2010

	Birr	Birr
Cash Flow from Operating Activities		
Profit before tax		(6,049,868)
Adjustment for :Depreciatio		1,232,943
Amortization		1,068,053
Provision for loans and advances		1,533,300
Cash flow before change in working capital		(2,215,572)
Increase in other assets	(12,216,168)	
Increase in loans and advances	(153,194,041)	
Increase in stocks	(2,971,754)	
Increase in creditors	35,796,699	
Increase in deposits	238,010,767	
Increase in refund to shareholders account	52,714	
		105,478,217
Cash flow from operating activities		103,262,645
Cash Flow From Investing Activities		
Purchase of fixed assets	(5,697,844)	
Investment in computer software	(1,046,268)	
		(6,744,112)
Cash Flow From Financing Activities		
Shares issued		12,529,830
Net cash increase for the period		109,048,364
Cash and bank balances at the beging of the period		87,819,167
Cash and bank balnces at the end of the period		**196,867,531**

Board Chairman

President

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.
BERHAN INTERNATIONAL BANK S.C.

የባለአክሲዮኖች 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ

ታህሳስ 2 ቀን 2003 ዓ.ም.

አጀንዳዎች፡-

1. አጀንዳችን ማጽደቅ፣
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አመታዊ ሪፖርት ማድመጥ፣
3. የውጭ ኦዲተሮችን አመታዊ የኦዲት ሪፖርት ማድመጥ፣
4. በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ክፍያ መወሰን፣
6. አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና የአክሲዮን ዝውውሮችን ማጽደቅ፣
7. የውጭ ኦዲተሮችን መሰየምና ክፍያቸውን መወሰን፣
8. ቃለጉባኤ ማጽደቅ፣

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

የዳይሬክተሮች ቦርድ